የረቡዕ ሰኔ 1 1997 ( የጁን 8 2005)

የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## መለስና አራት ካርዶቹ

በመጀመሪያ ላለፉት ጥቂት ሳምንታት በሀገራችን የፖለቲካ መልካ ምድር ውስጥ የተከሰተውን ሀቅ እንመልከት። በሚያዚያ ሠላሳ ቀን በዋለው ዕለተ-ሰንበት፥ በአዲስ አበባ ከተማ ማንም ያልጠበቀው፥ ያላሰበው፥ ያላዘጋጀው መሬት አንቀጥቅጥ ሠላማዊ ሰልፍ ተደርጎ የወያኔን ሥርዓት ከስር መሠረቱ አናጋው። ይህ ትዕይንተ-ሕዝብ ዳግማዊ የካቲትን ያስታወሰ ነበረ። በሀገራችን ስር ከሰደዱት የውጭ ሀገር የስለላ መረቦች በስተቀር፥ ስለዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ብዛትና መጠን የቅድሚያ እውቀት የነበረው ክፍል አለ ለማለት ያስቸግራል። መለስና ግበረ- አበሮችንም በድንገት ነበር የያዛቸው ለማለት ይቻላል። ይህም በመሆኑ መግቢያ ቀዳዳ ጠፍቶባቸው ሲርበተበቱ እንደነበር ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተሰወረ አልነበረም። ይህ ትዕይንተ-ሕዝብ በማንም ግፊትና ቅስቀሳ ሳይሆን በራሱ በሕዝቡ ምሬት፥ ሰቆቃና ለሥርዓቱም ካለው ጥላቻና ንቀት የመጣ ለመሆኑ አሌ የሚባል አይደለም። አሁንም እንደገና የሕዝብን ቁጣና ኃይል ማንም ሊገታው እንደማይችል ተረጋግጧል። ልብ ያለው ልብ ይበል። ልብ የነሳው፥ ይጎተታል እሬሳው፥ መባሉ አይቀሬ ነው።

በታህሳሥ 3 ቀን 1953 ዓም የሥርዓቱ መኮንኖች ባነሱት አመፅ በሬዲዮ ያሰሙት አንድ አባባል ነበራቸው፥ "ቀፎው የተነቀነቀበት ንብ ገንፍሎ ከወጣ የሚያቆመው የለም" ነበር ያሉት። እሳት ቢዳፈን የጠፋ እንደልሆነ ሁሉ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፥ ልክ እንደማንኛውም የዓለም ሕዝብ ፥ የራሱን ጊዜና ሁኔታ ተጠቅሞ ከአምባገነኖች ጭቆና መላቀቁ ታሪካዊ ዕውነት መሆኑ የሚያዚያው 30 ቀን ሰላማዊ ሰልፍ በተጨባጭ አስመስክሯል። ከዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ወዲህ፥ የሀገራችን የፖለቲካ መልከዓ-ምድር በመሠረታዊ መልኩ እየተለወጠ በመሄድ ላይ ይገኛል። የኃይሉ አሰላለፍም እየተበወዘ ነው ማለት ይቻላል። የተቃዋሚው ክፍልም በሁለት አጣብቂኝ ውስጥ እንደተጠራቀቀ ይታያል። በአንድ በኩል የሕዝቡ ሠላማዊ አመፅ- አርዕድ-አንቀጥቅጥ በመሆኑ፥ የሕዝቡን ግፊት መቻልና አለመቻል ሲሆን፥ በሌላ በኩል ደግሞ፥ እየተፍረከረከ በመሄድ ላይ ያለው ሥርዓት የመጨረሻ መፍጨርጨር በማድረግ ላይ ስለሆነ፥ የሱን የስለላ፥ የፕሮፓጋንዳና የድንፋታ ማስፈራሪያ መቋቋም መቻል-ወይም አለመቻል ነው። የተቃዋሚው ኃይል ከዚህ አጣብቂኝ ለመውጣት የሚችለው፥ በመጀመሪያ ደረጃ የመከላካያ ኃይሉን አጠንክሮ ሲገኝ ብቻ ነው። ይኸውም፥ ከምን ጊዜውም በበለጠ ኅብረቱን ማጠንከር ነው። የቅንጅቱና የኅብረቱ መሪዎች የሕዝብ ተገዥነታቸውን ማረጋገጥ ከፈለጉ፥ በግድ የሕዝቡን ወቅታዊ ጥያቄ መመለስ ሊኖርባቸው ነው። አሁን ያለውን የሕዝብ ቁጣ ወደ ሰላማዊ-ሕዝባዊ አመፅ በመለወጥ ሁኔታውን እያስተካከሉና

አቅጣጫ እየሰጡ የሕዝቡን የዴሞክራሲያዊ ትግል መምራትና ማቀናጀት፥ ታሪክ የጣለባቸው ተልዕኮና ብሔራዊ ኃላፊነት መሆኑን መዘንጋት የለባቸውም።

ዛሬ መለስና ግብረ-አበሮቹ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የተጠሉ፥ የተዋረዱና የተናቁ ብቻ ሳይሆኑ የተደፈሩም ናቸው።መንግሥት እንደ መንግሥት ከተደፈረ ደግሞ፥ ከዚያ በኋላ ምን እንደሚከተልበት ማወቅ አለበት። የነመለስ ትዕቢትና ድንቁርና ሞራ ግን የወቅቱን ሁኔታ እንዳያዩ ሸፍኗቸዋል። የሕዝቡን ሰላማዊ አመፅ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመፍታት ከመጣር ይልቅ፥ አሁንም ያው ያረጀ ያፈጀ እኩይ ድርጊታቸውን ለመፈፀም ነው እየተውተረተሩ ያሉት። የጎሳ ሽራቸውንም ለመጫወት ይፈልጋሉ። የትግራይ ሕዝብ ግን ጆሮ ነፍጓቸዋል። ከወገኑ ከቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ቆሞ የወያኔን ሥርዓት ለመገርሰስ በመታገል ላይ ይገኛል። ይህንን ሀቅ መለስ ዜናዊ በሚገባ ተረድተቶታል። ለዚህም ነው ሌላ ዘዴ በመፈለግ ደፋ ቀና እያለ ያለው። ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል አዘኔታም ይሁን ድጋፍ ማጣቱን በሚገባ የተረዳው በመሆኑ፥ ያላየውን ለመፈተን እየጣረ መሆኑ ይነገራል። በወቅቱ የሀገራችን የፖሊቲካ መድረክ፥ የሰማው እየሄደ ያልሰማው እየመጣ እንደሆነ ሁሉም የሚያየው፥ የሚታዘበው ክስተት ሆኗል። እንዳለመታደል እየሆነባት ነው መሰል፥ የኢትዮጵያን ኃብትና ንብረት በፈረቃ ለመቀራመት የሚፈጠሩ ፍጡራን አይጠፉም። ይህ ግን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዘላቂ ስትራተጂያዊ ጥቅም የሚፈይደው አንዳችም ጉዳይ አይኖርም። ከነመለስ ዜናዊ፥ ለኢትዮጵያ ስትራተጂያዊ ጥቅም የሚሆን ፋይዳ እንደማይመጣ ለአለፉት14 ዓመታት ለሁሉም ዜጋ ግልፅ ስለሆነ ፥ የወቅቱ ጥያቄና ትኩረት መሆን የሚገባው፥ ስለነመለስ ዜናዊ ባኅርይና ተግባር ማንሳትና መጣል ሳይሆን፤ የወያኔን ሥርዓት ለመተካት ምን ብሔራዊ አጀንዳ ይኖረናል የሚለው ነው። ይህንን ጥያቄ ጠይቆ የሚገኘው መልስ፥ ሀገራችንን ወደ 21ኛው ምዕተ ዓመት ሊያሸጋግራት የሚችል ብሔራዊ ዕቅድ ያመጣላታል ብለን እናስባለን። ለዚህም ተግተን እንሰራለን። መጀመሪያ ትኩረታችን ግን መሆን የሚገባው፥ ሀገሪቱን አሁን ካለችበት የወቅቱ የፖለቲካ አረንቋ ማውጣት ይሆናል። በዚህ ላይ ትኩረት ተደርጎ የተቃዋሚ ድርጅቶች እንዳይረባረቡ ለማድረግ አቅጣጫ አደናባሪ የሆኑ ጥንስሶች መኖራቸውን አስቀድሞ ማወቅ ይገባል። ተቃዋሚ ድርጅቶች በመሠረታዊ የሀገር ጉዳይ እንዳያተኩሩና በወያኔ መወገድ ላይ እንዳያነጣጥሩ፥ መለስና አሳዳሪዎቹ የተለያዩ ዕንቅፋቶችን ከመዘርጋት አይቆጠቡም። ይህንን መሰናክል አልፎ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥያቄ መመለስ የተቃዋሚ ድርጅቶች ኃላፊነትና ተልዕኮ መሆኑን ሕዝቡ ባደረገው የምርጫ ድምፅ አረጋግጦታል። ምርጫውን ለመከታተል የመጡ ምዕራባውያንም ታዛቢዎች መዝግበውታል። ካለ ስመ ፥ጥፉው ሚስተር ጂሚ ካርተር በስተቀር።

ይህን ተጨባጭ ሁኔታ መለሰና ግብረ-አበሮቹ እያንገፈገፋቸውም ቢሆን ሳይረዱት የሚቀሩ አይደሉም። ይህም በመሆኑ፥ መለስ አራት አካሄዶችን ለመጠቀም እየሞከረ ነው።

1. ችግሩ እየተባባሰና የሕዝቡ አመፅ/ ትግል የሚያስጨንቀው መሆኑን በዕርግጥ ከተረዳ፥ የሚወጠበትን ስልት ማዘጋጀት። አለቆቹ እንደሚመክሩት መውጫህን አዘጋጅ እንደ ማለት ነው። የመንግሥቱ ዓይነት አወጣጥና ኩብለላ እንዳይገጥመው ዘዴ ማመቻቸት። ከዚህም ጋር አያይዞ እስካሁን ሲያሸሸው የነበረው የሕዝብ ሀብት እንደተጠበቀ ሆኖ፥ ብዙ ኃብትና ንብረት እንደዚሁም ቅርቦቹን ጨርሶ የማሸሽ ጊዜ ማግኘት፥

2. ከኦነግና መሰሎቹ ጋር አዲስ ውይይት መክፈትና የጋራ አገዛዝ ብልሀትን መቀየስ፥ ይህንም ሲያደርግ የተለመደውን የዘር ርካሽ ፕሮፓጋንዳን መጠቀም፥ ወያኔንና ኦነግን ለማጥፋት ያሰፈሰፈ ኃይል ስለሚመጣ፥ ይህንን የጋራ ጠላት በጋራ መመከት አለብን ብሎ ለማወናበድ መሞከር፥ ይህ ግን ይሳካል አይሳካም ሌላ ጥያቄ ይሆናል።

3. ምዕራባውያንን ለማታለል፥ለሰላማዊ ሽግግር ስንል፥ ከተቃዋሚ ጋር በመወያየት ላይ ነን እያለ ጊዜ መግዛት፥ አያይዞም የህዝቡን ሰላማዊ አመፅ ለማኮላሸት መሞከር፥ ወዲያውም ከቻለ የተቃዋሚ ድርጅቶችን ለመከፋፈል መጣር፥ ኃይሉን ማሰባሰብና የተደናገጠውን ክፍል ማበረታታት፥ የተሸበረውን ማረጋጋት፥ ፥ ለዚህም ጊዜ የሚገኝበት ዘዴ ሁሉ መጠቀም። እንደገና ተጠናክሮ የሚወጣበትን ብልሀት መዘየድ።

4. እንዲያውም ከነጭራሹ፥ ያበጠው ይፈንዳ፥ (አነ ውደ አይቴ!) በማለት እንደገና በኃይል ለመግዛት የሚያስቸለውን ዕቅድ ማውጣት፥ የአስቸኳይ ጌዜ አዋጁን ላልተወሰነ ጊዜ ማራዘም፥ የሕዝቡን ሰላማዊ አመፅ ማኮላሸት፥ አደገኛ የሚላቸውን የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች ማሰር ማጥፋት፥ ሰብዓዊ መብቶቹን በሚያስከፋ መልኩ መጣስ፥ የፕሬስና የመገናኛ ብዙኃንን ማፈን። ወዘተ ይሆናል።

ከላይ የተዘረዘሩት አካሄዶች፥ ማነኛቸውም ለኢትዮጵያ እንደማይጠቅሙ፥መዘርዘር ያለብን አይመስለንም። የተነሳሳውን የሕዝብ አመፅ ማነኛቸውም የመለስ ካርዶች በዘለቄታ መልክ ሊያዳፍኑት ከቶ ሊገቱት እንደማይችሉ ግን በዕርግጠኝነት ልንናገር እንችላለን። እንዳይዳፈን ለማድረግ ግን፤ አሁንም የተቃዋሚ ድርጅቶች ከባድ ሀላፊነት የተላበሰ ትግል እንደሚጠብቃቸው መታወቅ አለበት። ትግሉን ለማፋፋም ደግሞ አስቀድሞ የሕዝቡን የልብ ትርታ ማዳማጥ፥ ማክበርና መከተል ያስፈልጋል።
ስለሆነም፦

- የሕዝቡ መነሳሳት ቀዝቃዛ ውሃ እንደይጨመርበት የወያኔን ርካሽ ፕሮፓጋንዳ እያከሸፉ ከሕዝብ ጎን መቆምና ሕዝቡን ማስተማር፥ የትግሉን አቅጣጫ መስመር ማሲያዝ፥
- ሰላምና ፀጥታ ደፍርሷልና የሕዝብን ደህንነት ለመጠበቅ ኃላፊነት አለብኝ በሚል ወያኔ፥ ጭፍጨፋ ለማካሄድ የሚመቸውን ምክንያት ማሳጣት፡ ከሕዝቡ ጋር አንድ አካል አንድ አምሳል ሆኖ መገኘት፥ መታየት፥
- ተቃዋሚ ክፍል የምርጫውን ጠቅላላ ሂደትና ሁኔታ ገምግሞ አዲስ የትግል ስልትና ስትራተጂ መንደፍ፥
- ሰላማዊ ሕዝባዊውን አመፅ ማፋፋም፥ የሰላማዊው ሕዝባዊ አመፅ፥ ከትጥቅ ትግል ያላነሰ መሥዋዕት መጠየቁን ተገንዝቦ ለዚያ ትግል መዘጋጀት።
- ከጎልፌተ- ወያኔ በኋላ ለምትሆነው ኢትዮጵያ የሚበጅ ብሔራዊ አጀንዳ ማዘጋጀት።
- ኅብረትን ማጠንከርና ለጥቅም አለመገዛት
- ለአገዛዙ ቀነ- ቀጠሮ ወይም ጊዜ አለመስጠት፥

ወያኔን ማለዘብ ይቸላል፥ በጎርፉም ሊለወጥ ይችላል፥ በማለት የሕዝቡን ዴሞክራሲያዊ ጥያቄና ሰላማዊ አመፅ ሊያኮላሹ የሚችሉ ክፍሎች፥ በዕርግጥ ዕርማቸውን ሊያወጡ የገባቸዋል። እነሆ ዛሬ አዲስ አበባ በከፍተኛ ውጥረትና ጭንቀት ላይ ትገኛለች፥ ከ1500 በላይ የሚሆኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪወች በኃይል እየተደበዱ ታፍሰው የት እንደገቡ አይታወቅም። የኮተቤ ነዋሪዎች የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ወደሰንዳፋ ይዞ የሚሄደውን የወታደር መኪና መንገዱን ዘግቶ ለብዙ ደቂቃዎች ያህል እንዳይሄድ ዘግቶት ቆይቷል። የሁለተኛ ደረጃ ት/ም ቤቶችም ተዘግተዋል። ይህ ሁኔታና ሂደት በየክፍለ- ሀገሩም እየተዛመተ ይገኛል። የከተማዋ ሱቆችና ንግድ መናህሪያዎች በራቸውን ቆልፈዋል። የወያኔ ታጣቂዎች ሰላማዊ ሕዝቡን እያስጨነቁ፥ እየደበደቡና እያሰሩ ናቸው። ያዋሳና የጎንደር ሕዝብ በማመፅ ላይ ይገኛል። ይህ ሁኔታ ወደ ድሬ ዳዋና በህር ዳር በመዘመት ላይ ይገኛል። ሁኔታው ከመለስ ዜናዊ ቀጥጥር እየሆነ በመሄዱ፥ ይህንም እንደ ምክንያት ተጠቅሞ ጭፍጨፋውን በስፋት እንደሚያካሂድ ምንም ጥርጥር አይኖርም።

ይህንን ሁኔታ የተቃዋሚ ድርጅቶች ኃላፊነትና ጥንቃቄ በተመላበት አካሄድ መያዝና መቆጣጠር ይጠበቅባቸዋል። አጥፍቶ ለመጥፋት የተዘጋጀውን የመለስ ዜናዊን የጥፋት ሂደት መከላከል አለባቸው። ሕዝብ እንዳያልቅ፥ የሰው ህይወት እንዳይጠፋ፥ ንብረት እንዳይወድም፥ ሀገር እንዳትጎዳ የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ አለባቸው። ታላቁ የኢትዪጵያ ሕዝብም በዘር በሃይማኖትና በጎጥ ሳይከፋፈል ከመቸውም በበለጠ እንደነቱንና ኅብረቱን ጠብቆ የወያኔን አጥፊ ተግባር ማክሸፍ አለበት። ይህ እንደ ቆሰለ አውሬ አደገኛ የሆነን የወያኔን ቡድን ለማስወገድ፥ ብልሀትና ጥበብን፥ አንድነትንና

ኅብረትን፥ አርቆ አስተዋይነትን ስለሚጠይቅ እያንዳንዱ ዜጋ በኅብረት መነሳት ወቅታዊና አስፈላጊ እናሳስባለን። ጥሪያችንን አናስተላልፋለን። መለስ እንደ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለመሸሽ ቢችልም፥ ሲሸሽ ግን ሕዝብ አበጣብጦ ፥ ሀገር አጥፍቶ ሊሆን ስለሚችል፥ ይህን ሁሉ ለመከላከል እያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት እንዳለበት እናስገነዝባለን፥ ጥሪያችንንም አናስተላልፋለን።

ትግላችንን እንቀጥላለን!!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል!!